የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)
www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

ግንቦት 18፤ 2010

# አሸባሪነት አያሻግርም

በኢሕአዴግ ውስጥ ሲስተናገድ የሰነበተው ትግልና መፋተግ፤ ጸጥታውን ሰብሮ ወደ አደባባይ ለመውጣቱ የቅዳሜው ውሎ አንድ ጉልህ ማሳያ ሆኗል። ሸንጎ ቀደም ሲል እንደጠቆመው በገዢው ግንባር ውስጥ በለውጥ ፈላጊዎችና በለውጥ አጋቾች መካከል ግብግብ ከተጀመረ ውሎ አድሯል። ይሁን እንጂ ትግሉ ይፋ ወጥቶ ለህዝብ እንዳይታይ ታምቆ ቢያዝም፤ በስርዓቱ ውስጥ የተፈጠረው ስንጥቅ እየሰፋ በመምጣቱ የውስጡ ወደ ውጭ መፍሰሱ የማይቀር ሆነ።

በአሁኑ ሠዓት የኢትዮጵያ ህዝብና የለውጥ ፈላጊው ቡድን እንደሚደማመጡና አይዞህ እንደሚባባሉ ያስተዋለው ለውጥ-አጋች ቡድን ወደ ተስፋ መቁረጥና ብሎም ወደ ጥፋት ተግባር እያዘነበለ መምጣቱን ታዝበናል። የቅዳሜው የቦምብ ፍንዳታ ለዚህ የጥፋት ተግባር ዓይነተኛ ምሳሌ ነው ። ይህ የጥፋት ተግባር ደግሞ በማንም ግለሰብ ይሁን ቡድን ቢጠነሰስ የአሸባሪነት ተግባር መሆኑ አያጠራጥርም። በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ ላይ ፈንጂ መጣል ምን ሌላ ስም አለው፤ ምንስ ሌላ ዓላማ ይኖረዋል? ንጹሃን የአገር ልጆችን መግደልና ማቁሰል ከባድ የወንጀል ሥራ ከመሆኑም ባሻገር፤ ሰብዓዊ ርኅራኄና መንፈሳዊ ጸጋ የጎደለው የጭካኔ ተግባር ለመሆኑ አያጠያይቅም።

አንድ በዚህ የሽብር ወንጀል ቆስላ ሆስፒታል የተኛች ወጣት እንዲህ ስትል ተናግራ ነበር፤ “ የደረሰብኝን ጉዳት ከምንም አልቆጥረው፤ ገና ለብዙ መስዋእትነት ተዘጋጅቻለሁ” ነው ያለችው። ይህ አነጋገር በዚያን እለት በመስቀል አደባባይ የተሰበሰበውን፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ፍላጎትና ዝግጅት በግልጽ የሚያስቀምጥ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። በዚህም ብቻ አያበቃም፤ ይህ አነጋገር ከጫፍ እስከ ጫፍ፤ ከትግራይ እስክ ኢሉባቦር፤ ክቤኒ ሻጉል እስክ ሐረር ያለውን የትዮጵያ ህዝብ ፍላጎትና ዝግጅት እንደሚገልጽ አንጠራጠርም። ስለሆነም ነው ይህ እኩይ ተግባር አሸባሪነት ነው ያልነው፤ ጥቂት ዜጎችን በመግደልና በማቁሰል፤ የጥፋት መልእክተኞችን ጭካኔ ከማሳየት አልፎ፤ የተጀመረውን የለውጥ አቅጣጫ ለመቀልበስ በፍጹም አይቻልም። ይልቁንም የዚህ ዓይነቱ ትንኮሳ በትግስትና በይቅርታ ታቅቦ ያለውን ህዝብ፤ የቁጣ ማእበል ቀስቅሶ ተንኳሾቹንና አጋሮቻቸውን እንዳይጠራርጋቸው እንፈራለን።

ሸንጎ እስካሁን በአሸባሪዎች ጥቃት የሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎችና ቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትና ብርታት እየተመኘን፤ ድርጊቱንም አምርረን እንደምናወግዝ እንገልጻለን። ከዚህም ባሻገር፤ በዶክተር አቢይና ቡድናቸው የተጀመረውን የለውጥ አቅጣጫ ሸንጎ እንደሚደግፍ እያስታወቅን፤ ለላቀ ዴሞክራሲና ዘላቂነት ላለው ሥርዓት ለውጥ እውን መሆን ሁሉንም በአገሪቱ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች የሚያሳትፍ የብሔራዊ መግባባት ሂደት በአስቸኳይ መከናወኑ ወሳኝ መሆኑን በድጋሚ ልናሳስብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያሸንፋል !!

ሽብርተኛነት አያሻግርም !!